# የአድዋ ድል፣ አፄ ምኒልክና ሥነ-ልቦናዊ ጥንካሬያቸው

በገዛኸኝ ድንቄ
ፍራንክፈርት ( ጀርመን )

ዓመት በዓመታት፣ ዘመን በዘመናት እየተተኩ ሲያልፉ የቀደምት የነጻነት ታጋይ ጀግኖቻችን ታሪክም በይበልጥ ጎልቶ ይወደሳል። በወርሃ የካቲት የአድዋ ላይ የድል በዓል ቀን ሲዘከር ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ወደር የማይገኝላቸው አያሌ ጀግኖችዋ መካከል በተለይም የአፄ ምኒልክ ስም ጎልቶ ከመሀል ብቅ ይላል። አዎን! አፄ ምኒልክ ስማቸውና ገድላቸው ሲነሳ አብሮ ምንጊዜም አድዋ ይነሳል።የአድዋ ላይ ድል ግኝት በሺ የሚቆጠሩ የቀደምት አያቶቻችን ደማቸውን እንደ ጅረት ያፈሰሱባትና አጥንታቸውንም ለነፃነታቸው ከስክስውበት፣ ክቡር ሕይወታቸውንም የሰውበት ውጤት ናት። የፖፕ ሙዚቃ አቀንቃኝዋ ድምፃዊት እጅጋየሁ ሺባባው(ጂጂ) ስለ  አድዋ አንዲህ ሲልም ታንጎራጉራለች ፣

የተሰጠኝ ሕይወት ዛሬ በነፃነት፣
ሰው ተከፍሎበታል ከደምና ከአጥንት፤
ስንቱ ቀን ወደቀ በነፃነት ምድር፣
ትናገር አድዋ ትናገር ትመስክር፤
ትናገር አድዋ ትናገር አገሬ፣
እንዴት እንደቆምኩኝ ከፊታችሁ ዛሬ፤

እልፍ ትልናም…  አድዋ ዛሬ ናት - አድዋ ትላንት ፣
መቼ ተነሱና የወዳደቁት?
ምስጋና ለነሱ ለአድዋ ጀግኖች፣
ለዛሬ ነፃነት ላበቁኝ ወገኖች።…

ለምኒልክ ከዛሬ 113 ዓመት በፊት ከፋሺስቱ የጣሊያን ወራሪ የጦር አበጋዞች ፊታኝ የህልውና ጥያቄ ገጠማቸው። ሁሌም በተለያዩ የውጭ ወራሪ ኃይላት ያልተደፈረች ኢትዩጵያን ከጣሊያን ቅኝ ገዢነት ሕልም ነፃ ማድረግ ወይስ ለቅኝ ግዛት ባርነት ሕዝባቸውን መዳረግ ለሚለው ፊታኝ የሕልውና ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ የሰጡና የአድዋንም ጦርነት በድል የተወጡ ጀግና መሪ በመሆናቸው ነው።

ታዲያ በፋሺስት ጣሊያን ወራሪ ጦር ላይ የአድዋ ድል መገኘት የአፄ ምኒልክ አመራር ውጤት ነው ካልን ምኒልክ ማን ናቸው? በሥነ-አካላቸውና በሥነ-መንፈሳቸውስ እንዴት ያሉ ሰው ነበሩ? ኢትዩጵያውያን የታሪክ ዘጋቢዎች እንደሚጠቁሙት ምኒልክ የተወለዱት በነሃሴ 12 ቀን 1836 ዓ.ም ነው። አፄ ምኒልክ ከአፄ ልብነ ድንግል ልጅ ፣ ከአቤቶ ያዕቆብ ትውልድ ሲያያዝ የመጡት የስመ ጥሩው ንጉስ የሳዕለ ሥላሴ የልጅ ልጅ የንጉስ ኃይለ-መለኮት ልጅ ናቸው። ትውልዳቸውም ከአቤቶ ያዕቆብ ጀምሮ ቢቆጠር አፄ ምኒልክ 13ኛ ይሆናሉ።

በ1848 ዓ.ም ንጉስ ኃይለ-መለኮት በሕልፈተ-ህይወት ሲለዩ አፄ ምኒልክ አባታቸውን በመተካት የሸዋ ንጉስ ሆኑ። ከዚያም አፄ ዩሐንስ ከድርቡሾች ጋር መተማ ላይ ሲፋለሙ ክፉኛ ቆስለው መጋቢት 2 ቀን 1881 ዓ.ም ሲያርፉ፣ አፄ ምኒልክ ከላይም የቀዳማዊ ምኒልክ ከታችም የልብነ-ድንግል ስርወ-መንግሥት ነበራቸውና የንጉስ ነገሥትነት ቦታቸውን ጥቅምት 25 ቀን 1882 ዓ.ም ያዙ።

ምኒልክ በቅርፀ አካላቸው ሞላ ያሉ፣ ረዘም ያለ ቁመና ያላቸው፣ ጠይም ፊታቸው ከጆሮሃቸው ጀምሮ እስከ አገጫቸው ዙሪያው በፂም የተከበበ፣ ረዘም ያለ ፊትና አማትሮ የሚመለከት ዓይን ያላቸው፣ ከንግሰ-ልብሳቸው ጋር የመሪነትን ክብረ ሞገስ የተላበሱ ፍጡር ነበሩ።

በሥነ ልቦናዊ ተፈጥሮሃቸው አፄ ምኒልክ ድፍረትን እንጂ ፍርሃትን የማያውቁ፣ ድልን እንጂ ሽንፈትን ያልተቀበሉ፣ ጀግንነት እንጂ መንበርከክ ያልገጠማቸው፣ ቆራጥ፣ ቆፍጣና፣ ኮስታራ፣ አትንኩኝ ባይና አርቆ አስተዋይነት ሰብህናም የተላበሱ ሰው ነበሩ።

በግል ሥነ ባሕሪያቸው ደግሞ ደግ፣ትሁት፣ ቻይና ታጋሽ፣ ይቅር ባይነትን የሚያውቁ እንዲሁም እንደ ንጉሥ አገራዊ ባሕልን አክባሪ፣ ሕዝባቸውንም አፍቃሪ ስለነበሩ፣ በአፀፋው ሕዝቡም ለሳቸው የነበረውን ፍቅርና ከበሬታ ለመግለፅ በቁልምጫ እምዬ ምኒልክ እያለ ይጠራቸው ነበር።

በዘርፈ ብዙ አገራዊ ጉዳዮች ላይም እንደ አለቃ ሳይሆን እንደ ሕዝብ አባት ችሮታቸውን ይለግሱ እንደነበር ታሪክ ይመስክርላቸዋል።
ከአፄ ምኒልክ ልዩ ሥነ-ልቦናዊ ተፈጥሮና ችሎታቸው አንዱ ብልህነትን የተካኑ፣ መንፈሰ-ግልፅ፣ ቅንነትን የተላበሱ፣ በራሳቸውም አነሳሽነት ኢትዮጵያን በዘመናዊ የሥልጣኔ ጎዳና ላይ ለማስገባት ከፍተኛ ራዕይ የነበራቸው መሪ ሆነዋል።ለአብነት ያህል መጥቀስ ቢያስፈልግ በኢትዮጵያ ት/ቤት፣ሃኪም ቤት፣ፖስታ ቤት፣ ባንክ እንዲከፈት፤የባቡር ሃዲድ፣ የመብራትና የስልክ መስመር እንዲዘረጋ፤ እንዲሁም የቀላል ኢንዱስትሪ ማምረቻ ድርጅቶች እንዲገነቡ መሠረት ጣይና የሥልጣኔ ጮራ ፈር ቀዳጅም ናቸው።
ምኒልክ በአመራር ዘመናቸው በሥነ-ልቦናዊ ተፈጥሮሃቸው ለራስ ዝቅ ያለ ግምት መስጠት፣ ከራስ መተማመን በላይ መሆን፣ ቅናት፣ ጨካኝነት፣ እብሪተኛነትና እኔ ብቻ አውቃለሁ ባይነት እንደ ዘመናችን ገዢዎች አልታየባቸውም።
ታዲያ የአድዋ ጦርነት እንዴት ተጀመረ? የግጭቱስ መነሻ በአፄ ምኒልክና በጣሊያን መንግስት መካከል ምን ነበር? የሚለውን ደግሞ ቀጥለን እስቲ እንመልከት።
አፄ ምኒልክና በኢጣሊያው ንግሥ ኡምቤርቶ ሙሉ ሥልጣን ተቀብሎ እንደራሴ ሆኖ በተሾመው ኮንት አንቶኔሊ መካከል ሚያዝያ 25 ቀን 1881ዓ.ም ውጫሌ ላይ የወዳጅነትና የንግድ ባለ ሃያ አንቀፅ ውል ይዋዋላሉ። ከነዚህ ውሎች ውስጥ ግጭትን የቀሰቀሰው 17ኛው አንቀጽ ነበር። በውሉ ላይ በ17ኛው አንቀጽ በጣሊያንኛ የተጻፈው የኢትዮጵያ ንጉሰ-ነገሥት የሚፈልጉትን ጉዳይ ሁሉ በጣሊያን መንግሥት በኩል ለመላላክ ፈቅደዋል የሚል ነበር። ምኒልክ ይህ ውል ፈፅሞ ሊዋጥላቸው አልቻለም፣ መንግስታቸውንና ሕዝባቸውን በጣሊያኖች የጥገኝነት መዳፍ ሥር የሚጥል ነበርና ነው።ብዙም ተከራከሩበት፣ ከናካቴው ይህ አንቀጽ ከውሉ ላይ እንዲሰረዝም በደብዳቤ መላልሰውም ተጻጻፉበት፣ ከጣሊያን መንግሥት በኩል ግን መልሳቸው ጆሮዬ ዳባ ልበስ ሆነ።
አፄ ምኒልክም በውጫሌው ውል በ17ኛው አንቀጽ ላይ የተጻፈውን የጥገኝነቱን ሃሳብ ለመፋቅ የጣሊያኖችን እምቢተኝነት ሲረዱ መኩዋንቶቻቸውን ሰብስበው እንዲህም አሉ “ ከንግዲህ ወዲህ ከጣሊያኖች ጋር የነበረኝን ወዳጅነት ትችያለሁ! የውጫሌውንም ውል አፍርሻለሁ!” አሉ። ደም እንዳይፈስ፣ ሕዝባቸውም እንዳይጎዳባቸው ብዙ ቢደክሙም ጦርነቱ ግን አይቀሬ ሆነ። በጄኔራል ባራቴሪ የሚመራው የጣሊያን ጦር የካቲት 22 ቀን ከሌሊቱ አስር ሰዓት ገደማ ሊነጋጋ ሲል እንዳአባ ገሪማ ደረሰና መድፉን ጠመደ።በዚህን ጊዜ ምኒልክ ደግሞ ጦራቸውን ከአገሪቱ አራቱም ማዕዘናት አሰባስበው ወደ አድዋ ተመሙ። ከዚያም በፉከራ ከአምባላጌ ላይ የተከላችሁትን ባንዲራ ነቅላችሁ ካልሄዳችሁ በስተቀር ከዚች ቦታ ላይ ፍንክች አልልም! ሲሉ አስጠነቀቁ።በዚህ ሂደት ውስጥ ከሌሊቱ 11 ሰዓት ላይ ጄኔራል አልቤርቶኒ በተሰማራበት የግራ ግምባር በራስ መንገሻ ዮሐንስ ጥበቃ ላይ ተኩስ ተጀመረ።ምኒልክም ከመቅፀበት ለሠራዊታቸው የታጠቅ! ትህዛዝ አስለፈፉ። የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ከማለዳው 12 ሰዓት ሠራዊቱ ባንድ አፍታ የጦርነት ትጥቁን ታጥቆ ቀፎው እንድተነካበት ንብ የቸኮለ በሌጣው፣ ያልቸኮለው በኮሪቻው እየተሰካ እየፎከረ፣ እየተንደቀደቀ ከጦርነቱ አውደ-ግንባር ገባበት። ምድርም ቀውጢ ሆነች፣ እቶነ - እሳትም ነደደባት ፣ ከዚያማ ወዲያ ምን ይነገራል...። የጣሊያን መድፍ ጬኸት በማለዳ የቀሰቀሰው የሸዋ ፈረሰኛ፣ የጎጃም እግረኛ፣ የትግሬ ነፍጠኛ፣ የኦሮሞ የጦር ስልተኛ፣ ከቦ ያናፋው፣ ይቀላው ያንገዳግደው ጀመር። ከነብር የፈጠነውና ሞት - አይፈሬው የኢትዮጵያ ሠራዊትም እንዲህ እያለ ይጮህና ይፎክር ጀመር...

ምናባቱ ጣሊያን - ኡምቤርቶ ምናባቱ ፣
ቢደነድን ባቱ - ቢሰፋ ደረቱ ፣
እንደ አረብ ግመል- ቢመዘዝ ቁመቱ፣
እንጨርሰዋለን በገዛ ጥይቱ ። እያለ በጥይት ፈጀው ፣ በያዘው ጎራዴም

የጣሊያንን ወታደር አንገት አንገቱን እየቀነጠሰ አሰጣው፣ ዘለሰው።በዚህ ሁኔታ ለስደስት ሰዓት ያህል ጦርነቱ ተፋፍሞ ሲያበቃ የጣሊያን ጦር ብርክ ይዞት በመጣበት መንገድ እግሬ አውጪኝ አለ።የጣሊያን የጦር ጄኔራሎች ሽጉጣቸውን እያጎረሱ፣ ጎራዴያቸውንም እየመዘዙ ሠራዊታቸውን „አትሽሽ !“ እያሉ ሊያስፈራሩት ቢሞክሩም እምቢ ብሎ እየጣሳቸው ነፍሴ አውጪኝ ሽሽቱን ቀጠለ። የጣሊያንን ጦር ሲመሩ ከነበሩት የጦር ጄኔራሎች መካከል ዳቦርሚዳ እና አሪሞንዲ በጦርነቱ ሲሞቱ፣ ከቆሰሉት 2 ጄኔራሎች ደግሞ አልቤርቶና ኤሊና መካከል ጄነራል አልቤርቶኒ ተማረከ።በስተመጨረሻም የጣሊያኑ ጦር አዛዥ የነበረው ጄኔራል ባራቲየሪ ሳይቀር ተማረከ።

አፄ ምኒልክም ጦራቸውን እየመሩ የቀረውን የጣሊያን ሠራዊት እያሳደዱ መረብን አሻገሩት። የተቀሩትም የጣሊያን ወታደሮች ወደ ጦራችን ላይ ሲተኩሱ የነበሩበትን ጠመንጃና መትረየስ አፈሙዙን ጨብጠው ሰደፉን ወደ ሰማይ እየሰቀሉ ተማረኩ።
የኢትዮጵያ ሠራዊት ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በመጣው የፋሺስት ጣሊያን ወራሪ ጦር ላይ ድልን ተጎናጸፈ። ጣሊያኖችም በደረሰባቸው ሽንፈት አንገታቸውን ደፉ። ድሉም በማያወላውል መንገድ የኢትዮጵያውያን ሆኖ ጦርነቱ እኩለ ሌሊት ገደማ ላይ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ተጠናቀቀ።
በጦርነቱ ፍልሚያ ላይ ከሁለቱም ወገን በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወታደሮች ቆስለዋል፣ ሞተዋል። የጣሊያን ጦር ተመክቶበት የመጣባቸውን 11ሺ ጠመንጃዎችና የያዙትም 56 መድፎች በሙሉ ተማርከዋል፣ ከነዚህም ውስጥ 18ቱ መድፎች ለአንድ ጊዜ እንኳዋን ሳይተኮሱባቸው ጥይታቸው እስከ መንኮራኩራቸው ወድቀው ተይዘዋል።
ጄኔራል ባራቲየሪ ከምርኮኝነቱ ተለቆ አገሩ ከገባ በኃላ ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ ሰጥቶ ነበር። "…እኛ የሰለጠነው ዓለም ስልጡን ወታደሮች ምንም አያውቁም ከሚባሉት ደፋሮች ኢትዮጵያውያን የምንማረው ትምህርት አለ። አበሾች ለባሩድና ለጥይት ይሳሳሉ፤ የሚገድሉ ካልሆነ በስተቀር አይተኩሱም። ለዚያውም ቢሆን አሥርና 15 ያርድ ያህል ቀርበው በአንድ ጥይት ደራርበው መግደል ይፈልጋሉ። ያለዚያ ተደበላልቀው በጎራዴ መምታትን ይመርጣሉ እንጂ ጥይት ማበላሸት አይወዱም። ይህም መሣሪያውን በማስጮህ ብቻ ጥይት ለሚያባክነው ለሰለጠነው አገር ወደር የሌለው ጥሩ ትምህርት ነው። …"
አዎ! አፄ ምኒልክ የአድዋን ጦርነት በድል ለመወጣት ጥሩ የጦር አዛዦችን እንደነ ፊታውራሪ ገበየሁ፣ ደጃዝማች በሻህ አቦዬ፣ ደጃዝማች ጫጫ(የጎላው ሻለቃ)…ወዘተ ዓይነት የቁርጥ ቀን ልጆች ምትክ የማይገኝለት ሕይወታቸውን ለአገራቸው ነፃነት፣ ለመሪያቸውም ክብር ሲሉ ራሳቸውን መስዋዕት ያደረጉ ታማኞችን ያፈሩ መሪ ናቸው።ስለ አድዋ ድል ሲነሳም ስለነዚህ ኢትዮጲያዉያን ጀግኖች ስም አብሮ ይታወሳል።ይህንንም አስመልክቶ እውቁ ባለቅኔና ደራሲ ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድኅን " እሳት ወይ አበባ " ተብላ በተሰየመችው የሥነ-ግጥሞች መድብል ሥራዎቻቸው ውስጥ " አድዋ " በተሰኘችዋ ግጥማቸው ጀግኖቻችንን እንዲህ ያስታውሳሉ…

ዋ! … አድዋ … ፣
አድዋ የትላንትናዋ፣
ይኸው ባንቺ ሕልውና፣
በትዝታሽ ብፅኅና ፣
በመስዋዕት ክንድሽ ዝና፣
በነፃነት ቅርስሽ ዜና ፣
አበው ተነሱ እንደገና።

ምኒልክ ከዛሬዎቹም ሆነ ቀደም ሲል ከነበሩት የኢትዮጵያ መሪዎች ለየት ያለ የአመራር ክህሎትን አሳይተዋል። ይኸውም ፦

1ኛ. ሕዝባቸውንም ሆነ ሠራዊታቸውን አስገድዶ ሣይሆን አሳምኖ በመምራት ያምኑ ነበር።
2ኛ. በጦርነቱ ጊዜ ከበታቾቻቸው ጋር በመመካከር ለጋራ ድል የጋራ ውሳኔ ሰጥተው የኢትዮጵያን አንድነትና የሕዝባቸውንም ነፃነት ማስከበር የቻሉ መሪ ነበሩ።
3ኛ. ለጠላት የተዛባና የተሳሳተ ወታደራዊ መረጃዎችን በማስተላለፍ እንዲዘናጋ በማድረግና በተቃራኒው ሠራዊታቸው ግን ለአገሩና ለነፃነቱ ቀናኢ እንዲሆን ጥረዋል።በተጨማሪም ምኒልክ በጦርነት ሂደት ውስጥ የስለላ ሥራ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ በትውልድ ብቻም ሣይሆን ልበ-ኢትዮጵያዊ የሆኑትን ገብረ-እግዚአብሔር እና አውሃሎም የሚባሉትን ሰላዮች ከጣሊያኖች ወገን ያዩትንና የሰሙትን መረጃ ሁሉ እየመጡ በምስጢር ማቀበል እንዲችሉ ተግባብተዋል።

ታሪክን የሚሰራው ሕዝብ ነው ቢባልም፣ ግለሰቦችም ታሪካዊ ሚናን በአመራር ውስጥ ይጫውታሉ።ዛሬ በአገራችን አንድነታችን፣ ነጻነታችን፣ብሔራዊ ማንነታችንና ኩራታችን፣ ሉዓላዊነታችን አደጋ ላይ በወደቀበት ሰዓት…እምዬ ምኒልክ ና ወንዱ ና ወንዱ፣
ላንተ ጌጥህ ነበር ጠላት ማሳደዱ። …ያሰኛል
የማሲንቆው አምባሳደር ድምፃዊው ሻምበል በላይነህ "ኑሪልኝ ሃገሬ' ዘፈኑ ላይ እንዳቀራረው..። የአድዋ ድል የትላንቱም፣የዛሬውም፣የነገውም ኢትዮጵያዊ ትውልድ መኩሪያ ብቻ ሳይሆን

የአፍሪካውያን እንዲሁም የመላው ዓለም ጥቁር ሕዝብ የነጻነት ምልክትና የኩሩ ትውልድ ቅርስም ነው።ታሪክንና አገርንም የሚጠብቀው ትውልድ ነው። ከትውልድም አዲሱ ትውልድ ነው።
የሥነ-ልቦና ጥናት ምርምሮች እንደሚያስረዱት ታላላቅ መሪዎች ታላቅና ጥራት ያለው ገፀ - ሰብህናን የተላበሱ ናቸው። በዓለማችን ላይ ትላልቅ ሥራዎችንም የሰሩ ሰዎች በትላልቅ ፈተናዎች ውስጥ ነጥረው የወጡ ናቸውና።
የአፄ ምኒልክ ሥነ-ልቦናዊ ጥንካሬና የገፀ - ሰብህና ጥራትም ለነፃነታቸው ዘብ መቆም ለቻሉ ኢትዮጵያውያን ፣ አፍሪካውያን ፣ እንዲሁም መላው ጥቁር ሕዝብ የሕሊና ነፃነት ታጋዮች የመልካም አርሃያ ተምሳሌት ናቸው። ኔልሰን ማንዴላም ፣ ኩዋሜ ንክሩማም ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግም ፣ ማልኮልም ኤክስም ፣ ካርል ስቶክስ ፣ ጄሲ ጃክሰን ፣ ባራክ ኦባማም..የዚሁ ትግል ውጤት ናቸው። አፄ ምኒልክ የጥቁር ሕዝቦች የአካልና የሕሊና ነፃነት ታጋዮች ሁሉ ሥነ - ልቦናዊ ጥንካሬያቸው ፈርጥሞ እንዲወጣ ፈር ቀዳጅ ናቸው።

ዓመተ ምህረቶቹ በኢትዮጲያ ዘመን አቆጣጠር ናቸው ።

አንባቢው ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ በኢሜይል አድራሻው፣
gez.dinku2@googlemail.com ገንቢ ኃሳቦችን መላክ ይችላል።